## <u>የ8ተኛው የአርብቶ አደሮች ቀን በዓል ላይ</u>

## <u>የኢትዮጵያ የአርብቶ አደሮች የጋራ አቋም መግለጫ</u>

"መልካም አስተዳደር ለአርብቶ አደር ዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ በጋራ እንሥራ" በሚል መዕከላዊ ጭብጥ ዙሪያ እየተከበረ ያለው 8ተኛው የኢትዮጵያ የአርብቶ አደሮች ቀን በመዲናችን አዲስ አበባ ክቡር ጠ/ሚኒስትሩን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣትና የአርብቶ አደሩ አጋር የልማት አካሎች በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ በመከበሩ የተሰማንን ከፍተኛ ደስታ ለመግለፅ እንወዳለን።

ቀደም ሲል ከ1ኛ እስከ 7ኛ በተከታታይ በየክልሎቹ ሲከበር በቆየው የአርብቶ አደር ቀን በዓላት ተነስተው የነበሩ በርካታ ጥያቄዎች በየደረጃው በመንግስት *በኩል ምላሽ* ተሰጥቷል። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንጠቅሳለን።

1 .በአገራችን አርብቶ አደሩ፤ እንደ አንድ የአገሪቱ ማህበረሰብ መታወቁ፣

2. ለአርብቶ አደሩ የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመቅረፍ መንግስት በሰጠው ትኩረት ተቋማዊ ምላሽ ማግኘት መቻሉ፣

3. የአርብቶ አደር ቀን በብሔራዊ ደረጃ በመንግስት ካላንደር ገብቶና ቦታ ተሰጥቶት ለማክበር በጠቅላይ ሚኒስተራችን ቃል መገባቱ፣

4 በልማቱ መስክ የአርቶ አደር ማህበረሰብ ፕሮጀክትን ጨምሮ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን የግል ባለሀብቶችን በማስተባበር የአርብቶ አደሩን ህይወት ለመቀየር የሚያስችሉ ጅምርና አበረታች ስራዎች መታየታቸው የሚጠቀሱ ናቸው።

ከዚህ በላይ የጠቀስናቸውና በጥሩ አብነታቸው የምናነሣቸው ወደፊትም በስፋት እንዲቀጥሉ እየጠየቅን ከችግሩ ውስብስብነትና ስፋት አንፃር በርካታ ስራዎች ትኩረት በዚሁ መሠረት የሚከተሉት ባለ አስራ አራት ነጥብ የአቋም መግለጫ አውጥተናል።

1. የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲው ከአርብቶ አደሩ ተጨባጭ የአኗኗር ዘይቤ ጋር ተቃኝቶ የሚተገበርበት ሁኔታ እንዲመቻች፣

2. አርብቶ አደሩ የእንስሳት ልማቱንና ገበያውን በሚመለከት የተጀመሩ በጎ ጅምሮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣

3. የአርብቶ አደሩ ተጨባጭ የአኗናር ሁኔታ በተለይም የእንስሳት ሀብቱ መሠረት በማድረግ ሲጠየቅ የነበረው የብድር አገልግሎት በመንግስት በኩል ተጠንቶ ምላሽ እንዲሰጠው፣

4. የአርብቶ አደሩ ማህብረሰብ ቁልፍ ችግር የሆነው የእንስሳትና የሰው የውሃ አቅርቦት ልማት ይበልጥ ሊተኮርበት የሚገባ አብይ የልማት መስክ ጋር በሚጣጣም መልኩ የልማቱ ባለቤት የሆነውን አርብቶ አደሩን ባሳተፈ መልኩ እንዲሰራ እንጠይቃለን፣

5. በአርብቶ አደር አካባቢ የሚከሰተውን ግጭት በዘላቂነት ለመፍታት መንግስት በማድረግ ላይ ያለውን ጥረት አጠናክሮ እንዲቀጥል፣

6. በክልሎች መካካል የተጀመረው የልማት ትብብርና ተሞክሮ ተጠናክሮ የሚቀጥልበት ሁኔታ እንዲመቻች፣

7. ለመልካም አስተዳደርና ለዘላቂ ልማት ካለው አስተዋፅኦ አንፃር መንግስት ለአርብቶ አደር አካባቢዎች እየሰጠ ያለው የአቅም ግንባታ ሥራ እንቅስቃሴ በተለየ መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን፣

8. እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የፌዴራል መንግስት ለክልሎች እየሰጠ ያለው የልማትና የመልካም አስተዳደር ግንባታ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንጠይቃለን፣

9. በአርብቶ አደር አካባቢ በመንግስት በማካሄድ ላይ ያሉ አበረታች ጅምር የመሰረተ ልማት ስራዎች በተለይም በመንገድ፣ በቴሌኮሚኒኬሽን፣በመብራት ሀይል ወዘተ የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች፣

10. በአርብቶ አደር አካባቢ በማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ በተለይም በትምህርትና በጤና ረገድ ያሉብንን ችግሮች በመምህራን አቅርቦት በጤና ባለሙያዎች በመድሐኒት የተሟላ አገልግሎት ሊሰጡ በሚችል መልኩ የፌዴራል ተቋማት አስፈላጊ እገዛ እንዲያደርጉ፣

11. ቀጣዩ የአርብቶ አደር ቀን አከባበርን በተመለከተ በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአርብቶ አደር ቋሚ ኮሚቴና በፓስቶራሊስት ፎረም ኢትዮጵያ በጋራ የተቋቋመው አካል ቀጣዩን በዓል እንዲያመቻች እንጠይቃለን፣

12. በክልሎች የአርብቶ አደር ጉዳዮች ራሱን የቻለ አደረጃጀት ከክልል እስከ ቀበሌ የተጠናከረ ስለሆነ በዚሁ መንፈስ የፌዴራል መንግስቱም በፌዴራል አስፈፃሚ አካላት የተደራጀው የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር እና የልዩ ዕገዛ ቦርድ የአርብቶ አደር ሚኒስተር ሆኖ እንዲደራጅ፣

13. በአርብቶ አደር አካባቢ ለሚካሄዱ የልማት ፕሮግራሞች መሳካት በሙሉ አቅማችን በቀጥተኛ ተሳትፎ ከግብ ለማድረስ ቃል እንገባለን፣

14. በሕገ መንግስታችን የተገኘውን የብሔርና የብሔረሰቦች መብት ለማደናቀፍ የሚንቀሣቀሱ ማንኛውም ሀይሎች ከመንግስት ጋር በመሆን በፅናት እንታገላለን በመጨረሻም ይህ የአርብቶ አደር በዓል ዕውን እንዲሆንና በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር የበኩላቸውን ሚና ለተጫወቱ ሁሉም ወገኖች የላቀ ምስጋና እናቀርባለን፡፡

ትኩረት ለአርብቶ አደር ልማት

እናመሰግናለን

ጥር 18/1998

አዲስ አበባ